የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት/ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት ሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘዋል፡፡

- የተጠቃለለ የሂሣብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀትና በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደርን አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ገቢ፤**

1. የዱባይ ኤምባሲ የውጭ ምንዛሬ የገቢ ደረሰኝ ቁጥር 795401-795450 ከያዘው ጥራዝ ውስጥ ቁጥር 795450 የገቢ ደረሰኝ ባለመገኘቱ በደረሰኙ የተሰበሰበውን የገቢ መጠን ለማወቅ አልተቻለም፡፡

**ወጪ፤**

2. በዋናው መ/ቤት ብር 1,136,442.65 ለመጋረጃ ግዥ ወጪ የተደረገ ሲሆን ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ በቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ በመገኘቱ መመሪያው ከሚፈቅደው ውጭ ግዥ የተፈጸመ ከመሆኑም በላይ መ/ቤቱ ለከፈለው ገንዘብ ተወዳዳሪ ዋጋ ማግኘቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

3. በዋናው መ/ቤት ለጀነሬተር ጥገና የተከፈለ ብር 10,000.00 እና ለሰራተኛ ጫማ የተገዛበት ብር 114,350.00 በድምሩ ብር 214,350.00 በወጪ የተያዘ ሲሆን፤ ከአቅራቢዎች የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በቀጥታ ግዥ በመፈፀሙ መመሪያው ከሚፈቅደው ውጭ ግዥ የተፈጸመ ከመሆኑም በላይ መ/ቤቱ ተወዳዳሪ ዋጋ በማግኘት ግዥ መፈፀሙን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

4. ለመ/ቤቱ አገልግሎት ላልዋለ የመስተንግዶ እና የአየር ትኬት ግዥ ብር 209,261.23 ወጪ ሆኖ ክፍያ ተፋጽሞ ተገኝቷል፡፡

5. መ/ቤቱ የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት አስተዳደር ኮሚሽንን በማስፈቅድ በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር አዋጅ መሠረት የኮንትራት ሰራተኞች ቅጥር መፈጸም ሲገባው አለአግባብ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996ን መሰረት አድርጎ የኮትራት ሠራተኞች የቅጥር ውል በመፈፀሙ ከህዳር 10/2011 ጀምሮ ከተለያዩ ኤምባሲዎች ወደ ዋናው መ/ቤት ተመልሰው ለተሰናበቱ እና መመለስ ላልፈለጉ ሰራተኞች በሚል ተቀባይነት የሌለው የብር 10,512,082.55 የካሳ ክፍያ ፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

6. በድምሩ ብር 11,440,472.41 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች ተገኝተዋል፡፡

7. የበጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ ለ2011 በጀት ዓመት ከተደለደለው በጀት ብር 792,831.92 ክፍያ ተፈፅሞ በመገኘቱ የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ አለአግባብ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡

8. ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተያዘ በድምሩ ብር 200,164.76 ተገኝቷል፡፡

9. ለውሎ አበል ወጪ የሆነ ብር 219,472.83 ክፍያው ለመፈፀሙ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

10. ለተለያዩ የአገልግሎትና የዕቃዎች ግዥ የተከፈለ በድምሩ ብር 1,591,614.74 ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

11. የመ/ቤቱ ሰራተኞች ለመሆናቸው ማረጋገጫ ሳይቀርብ ብር 11,790,057.21 የደመወዝ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

12. ለውሎአበልና ለአገልግሎት ግዥ አለአግባብ ክፍያ በመፈፀሙ ብር 87,386.64 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል።

13. ለሚኒስትር መኖሪያ ቤት ለጀነሬተር የሚውል 1,400 ሊትር ነዳጅ ግዥ በብር 22,882.86 ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

14. ከቤት አበል ተቀናሽ ያልተደረገ ሥራ ግብር ብር 6,300.00 ተገኝቷል፡፡

**ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

15. በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 70,568,481.40 ተሰብሳቢ ሂሳብ በመገኘቱ ሂሳቡ የሚሰበሰብበት ወይም የሚወራረድበት እድል እንዲመናመን አድርጓል፡፡

**ተከፋይ ሂሳብ፤**

16. በወቅቱ ያልተከፈለ ብር 11,547,850.68 ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

**በጀት፤**

17. በህግ በተቀመጠው መሠረት የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ከካፒታል በጀት ብር 42,746,187.14 ከተደለደለው በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 17 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም።

## ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፤

18. ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንደሚተካ እየተገለፀ በተለያዩ ጊዜያት ከሚ/ር መ/ቤቱ በጀት ለተፈፀሙ ክፍያዎች ወጪ የተደረገ በድምሩ ብር 15,972,368.66 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በቀጥታ በወጪ ተይዞ መገኘቱ ታውቋል፡፡

19. የስጦታ አሰጣጥ መመሪያ ሳይኖርና ለማን ምን እንደሚሰጥ ግልፅ አሠራር ሳይዘረጋ ለስጦታ በሚል ብር 1,332,095.97 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለወደፊቱ መመሪያ ተዘጋጅቶና በሚመለከተው አካል ሳይፀድቅ እንደዚህ ዓይነት ክፍያዎች እንዳይፈፀሙ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

20. የመስሪያ ቤቱ የተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚጠቀሙበት የመደበኛ የስልክ መስመርና ኃላፊዎች ለሚጠቀሙበት የቀጥታ ሞባይል መስመር ስልኮች በስራ አመራሩ የተወሰነ የስልክ የክፍያ ተመን አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡

21. ከመደበኛ በጀት ብር 159,606,423.49 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 28,789,831.10 በድምሩ ብር 188,396,254.59 ስራ ላይ ያልዋለ ተገኝቷል፡፡

## ሌሎች ጉዳዮች፤

- የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የውስጥ ኦዲት ክፍል በመ/ቤቱ መዋቅር መሰረት ለክፍሉ የሚያስፈልገው የሰው ሃይል 18 ቢሆንም በክፍሉ በሥራ ላይ የሚገኙ 6 ኦዲተሮች ብቻ መሆናቸው እና እስከ ሰኔ 30/2011 የዋና መስሪያ ቤቱን ሂሳብ ኦዲት ያላደረገና ሪፖርት ያላቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

መሰረት ዳምጤ
የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር